ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ(አንድነት) ፓርቲ

ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን

የተላለፈ የመልካም ምኞት መግለጫ

በተለያየ ምክንያት ከምትወዷት ሀገራችሁ፣ ከወላጆቻችሁ፣ ከወዳጅ ዘመዶቻችሁና አብሮ አደጎቻችሁ ተለይታችሁ በመላው ዓለም እንደጨው ዘር ተሰራጭታችሁ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን ሁሉ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በቅድሚያ እንኳን ለ2001 አዲስ ዓመት ለመድረስ በቃችሁ በማለት የመልካም ምኞት መልዕክቱን እነሆ ሲል በታላቅ አክብሮት ነው።

አንድነት ሕጋዊ ዕውቅናውን በአገኘበት በአሁኑ ወቅት ላይ ሆኖ ወደ ኋላ ሲመለከት የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን በአደረገው ሠላማዊ ትግል ውስጥ ከሀገር ውጭ ሆናችሁ ያደረጋችሁትን ትግልና የከፈላችሁትን ሁለንተናዊ መስዋዕት በሚገባ የስታውሰዋል።

መሪዎቻችን በታሰሩበትና ምልኣተ ሕዝቡ በሀገር ቤት ለከፋ ችግር በተዳረገበት በዛ መራራ ወቅት ያደረጋችሁትን ተጋድሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሕዝባችሁ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ እውን ለማድረግ የሚደረገውን ትግል አንድ ወሳኝ ርምጃ ወደፊት አስኪዳችሁታልና አንድነት ከልብ ኮርቶባችኋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት በማድረጉ ትግል ዋናው ተዋናይ በትግሉ ሜዳ ላይ የሚገኘው የሀገር ቤቱ ሕዝብ እንደሆነ ቢታወቅም እናንተ በውጭ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን/ኢትዮጵያዊያት ለድሉ መሳካት የምታደርጉት አስተዋጽኦ ወሳኝ ነው። ከዚህ በፊት የሠራችሁትን ታሪክ በላቀ ውጤት ትደግሙታላችሁ የሚል ጽኑ እምነት አለን።

አንድነት በቅንጅትነቱ ቆሞላቸው ለነበሩ ዓላማዎች ዛሬም የታመነና እስከመጨረሻው ለመቆም ቆርጦ የተነሣ መሆኑን በሀገር ውስጥ ላለ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል እንደገባ ሁሉ ለእናንተም ይህንኑ ቃሉን ያረጋግጣል።

ከዚህ በፊት በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረው ጊዜያዊ የውስጥ ችግር በሁላችንም ልብ ውስጥ ያሳደረውን ጉዳት አንድነት ይገነዘባል። ሆኖም አንድነት ካለፈው ችግሩ እየተማረ የወደፊት ትግሉን በአዲስ መንፈስ ለመቀጠል በቆራጥነት እንደተነሳ ሁሉ እናንተም በዚሁ መንፈስና በአዲስ ተስፋ ተነሳስታችሁ ከዚህ በፊት ያደረጋችሁትን ትግል አሁንም ከአንድነት ጋር በመሆን አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉበት አንድነት ጥሪውን ያስተላልፋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት

በውል ይረጋገጣል!

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ (አንድነት) ፓርቲ

ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ